ውድ ወላጅ/አሳዳጊ፡-

ልጆች ለመማር ጤናማ ምግብ ይፈልጋሉ፡፡ **DeKalb County ት/ቤት አውራጃ** በሁሉም የትምህርት ቀናት ጤናማ ምግብ ያቀርባል፡፡ ተማሪዎች በሚከተሉት ዋጋ፡ ምሳ $2.75 ለመጀመሪያ ደረጃ፣ $2.90 መካከልኛ ደረጃ፣ $2.85 ለሁለተኛ ደረጃ እና ቁርስ $1.60 ለመጀመሪያ ደረጃ እና $1.70 ለመካከለኛ/ሁለተኛ ደረጃ፡፡ ልጆችዎ ነጻ ወይም ቅናሽ ምግብ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ቅናሽ ዋጋው ለቁርስ $.30 እና ለምሳ $.40 ነው፡፡ ይህ ጥቅል የሚያካትተው የነጻ ወይም ቅናሽ ዋጋ ምግብ ጥቅማ-ጥቅም ማመልከቻ እና ዝርዝር መረጃ ነው፡፡ የማመልከት ሂደቱን ለማገዝ ከስር አንዳንድ የተለመዱ ጥያቄዎች እና መልሶች ይገኛሉ፡፡

1. ***ነጻ ወይም ቅናሽ ዋጋ ምግብ የሚያገኘው ማን ነው ?***

- ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ከ SNAP፣ FDPIR ወይም TANF ጥቅማ-ጥቅም የሚያገኙ ሁሉም ልጆች ለነጻ ምግብ ብቁ ናቸው፡፡
- በህግ በተደነገገ ወይም በፍርድቤት የማደጎ ቤት እንክብካቤ ስር የሚኖሩ የጉዲፈቻ ልጆች ብቁ ናቸው፡፡
- በት/ቤታቸው አዲስ ጀማሪ መርሀግብር ላይ የሚሳተፉ ልጆች ነጻ ምግብ ያገኛሉ፡፡
- ጎዳና ተዳዳሪ፣ የጠፉ ወይም ስደተኛ የሚባሉ ልጆች ነጻ ምግብ ያገኛሉ፡፡
- የቤትዎ ገቢ በፌደራል ገቢ ብቁነት መመሪያ ላይ ባለው ገደብ ውስጥ ከሆነ ልጆችዎ ነጻ ወይም ቅናሽ ዋጋ ምግብ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ የቤትዎ ገቢ በዚህ ሰንጠረዥ ላይ ባለው ገደብ ላይ ወይም በታች ከሆነ ልጆችዎ ለነጻ ወይም ቅናሽ ዋጋ ምግብ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

| የቤተሰብ መጠን | በአመት | በየወሩ | በወር ሁለቴ | በየሁለት ሳምንቱ | በየሳምንቱ |
|---|---|---|---|---|---|
| **1** | $23,606 | 1,968 | 984 | 908 | 454 |
| **2** | 31,894 | 2,658 | 1,329 | 1,227 | 614 |
| **3** | 40,182 | 3,349 | 1,675 | 1,546 | 773 |
| **4** | 48,470 | 4.040 | 2,020 | 1,865 | 933 |
| **5** | 56,758 | 4,730 | 2,365 | 2,183 | 1,092 |
| **6** | 65,046 | 5,421 | 2,711 | 2,502 | 1,251 |
| **7** | 73,334 | 6,112 | 3,056 | 2,821 | 1,411 |
| **8** | 81,622 | 6,802 | 3,401 | 3,140 | 1,570 |
| | +8,288 | +691 | +346 | +319 | +160 |

2. ***ልጆቼ የጎዳና ተዳዳሪ፣ ስደተኛ ወይም የጠፉ የሚባሉ እንደሆኑ እንዴት አውቃለሁ***? የቤተሰብዎት አባላት ቋሚ አድራሻ የላቸውም? የሚኖሩት በመጠለያ፣ ሆቴል ወይም ሌላ ጊዜያዊ መኖሪያ ውስጥ ነው? ቤተሰብዎት በየወቅቱ መኖሪያ ይቀይራል? የቀድሞ ቤተሰባቸውን ወይም ቤታቸውን ለመተው የመረጡ ማንኛውም ልጆች አብረዎት ይኖራሉ? በቤትዎ የሚኖሩ ልጆች ይህንን መስፈረት ያሟላሉ ብለው ካመኑ እና ልጆችዎ ነጻ ምግብ ያገኛሉ ተብለው ካልተነገረዎት እባክዎ Sonja Toblerን በ 678-676-2017 ወይም በኢሜል sonja_d_tobler@dekalbschoolsga.org ያነጋግሩ፡፡
3. ***ለእያንዳንዱ ልጅ ማመልከቻ መሙላት አለብኝ? አይ፡፡*** ቤትዎ ውስጥ ላሉ ሁሉም ተማሪዎች አንድ የነጻ እና ቅናሽ ዋጋ የት/ቤት ምግብ ማመልከቻ ይጠቀሙ፡፡ ያልተሟላ ማመልከቻ አንቀበልም፤ ስለዚህ ሁሉንም አስፈላጊ መረጃ ይሙሉ፡፡ የተሞላውን ማመልከቻ ለሚከተለው ይላኩ: ***በትንሹ ልጅዎት(ዎችዎት) ት/ቤት የት/ቤት አመጋገብ ሀላፊ፡፡***
4. ***በዚህ የትምህርት አመት ልጆቼ የነጻ ምግብ እንደሚያገኙ የሚገልጽ ደብዳቤ ካገኘሁ ማመልከቻ መሙላት አለብኝ? አይ፤*** ይህ ለአዲሱ የትምህርት አመት በመንግስት የተረጋገጠ መሆኑን ይገልጻል፡፡ እባክዎ ***ያገኙትን*** ደብዳቤ በጥንቃቄ ያንቡ እና መመሪያውን ይከተሉ፡፡ በቤትዎ ከሚኖሩ ልጆች ማንኛውም በብቁነት ማስታወቂያው ላይ ካልተካተቱ እባክዎ ስማቸውን ይጨምሩ እና መልሰው ለትንሹ ልጅዎት ት/ቤት ይላኩት፡፡ ጥያቄ ካለዎት የልጅዎ ት/ቤት የት/ቤት አመጋገብ ሀላፊን ያነጋግሩ፡፡
5. ***ኦንላየን ማመልከት ይችላሉ? አዎ።*** ማመልከቻ በወረቀት ከመሙላት ይልቅ ኦንላይን መሙላት ይበረታታል፡፡ የወረቀት ማመልከቻ ***ከልጅዎት ት/ቤት የት/ቤት አመጋገብ ሀላፊ*** ማግኘት ይችላሉ፡፡ የኦንላይም ማመልከቻው ተመሳሳይ መስፈርቶች አሉት፤ የወረቀት ማመልከቻው ላይ የሚጠየቁት መረጃዎች በተመሳሳይ ይጠየቃሉ፡፡ የኦንላይን ማመልከቻ ሂደቱን ለመጀመር ወይም የበለጠ ለማወቅ **https://schoolcafe.com** ይጎብኙ፡፡ ስለኦንላይን ማመልከቻ ወይም የወረቀት ማመልከቻ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት Tansheila Harris ን በ 678-676-1777, 678-676-1778 ወይም በኢሜል tansheila_harris@dekalbschoolsga.org ያነጋግሩ፡፡
6. ***የልጄ ማመልከቻ ባለፈው አመት ተቀባይነት አግኝቶ ነበር፡፡ አዲስ መሙላት አለብኝ? አዎ።*** በየአመቱ አዲስ ማመልከቻ መሞላት አለበት፡፡ የባለፈው አመት ማመልከቻ የ30 ቀናት የእፎይታ ጊዜ አለው፡፡ የአዲሱ ማመልከቻ ማስገቢያ ቀነ-ገደብ ሴፕቴምበር 29/2020 ነው። በት/ቤት ሰራተኛ የጸደቀ አዲስ መመልከቻ ካላኩ ወይም ልጅዎት ለነጻ ምግብ ብቁ መሆኑ ካልተነገረዎት ልጅዎት የምግቡን ሙሉ ዋጋ ይከፍላል፡፡
7. ***WIC አገኛለሁ፡፡ ልጆቼ ነጻ ምግብ ማግኘት ይችላሉ?*** WIC ውስጥ የሚሳተፉ ቤት ውስጥ ያሉ ልጆች ለነጻ እና ቅናሽ ዋጋ ምግብ ብቂ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እባክዎ የተሟላ ማመልከቻ ይላኩ፡፡
8. ***የምሰጠው መረጃ ይታያል? አዎ።*** ሪፖርት የሚያደርጉትን የቤተሰብ ገቢ የጽሑፍ ማስረጃ እንዲልኩልን ልንጠይቅዎ እንችላለን፡፡
9. ***አሁን ብቁ ካልሆንኩ ቆይቼ ማመልከት እችላለሁ? አዎ፤*** በትምህርት አመቱ በማንኛውም ሰአት ማመልከት ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ስራ-አጥ የሆኑ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ያላቸው ልጆች የቤቱ ገቢ ከገቢው ገደብ በታች ከወረደ ለነጻ እና ቅናሽ ዋጋ ምግብ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
10. ***ስለማመልከቻዬ በት/ቤቱ ውሳኔ ባልስማማስ?*** የትምህርት ቤቱን ባለሥልጣን Tansheila Harris በ 678-676-1777 ሊያነጋግሩ ይችላሉ፡፡ በ **(678-676-1786)** በመደወል ወይም ለሚከተለው በመጻፍ አቤቱታ እንዲሰማ መጠየቅ ይችላሉ: ***ዶ/ር Connie R. Walker፣ ዋና ዳይሬክተር፣ የDeKalb ት/ቤት አመጋገብ አገልግሎቶች፣ 1701 Mountain Industrial Boulevard, Stone Mountain, Ga. 30083***
11. ***ቤቱ ውስጥ ያለ ሰው የ U.S. ዜጋ ባይሆን ማመልከት እችላለሁ? አዎ።*** ለነጻ ወይም ቅናሽ ዋጋ ምግብ ለማመልከት እርስዎ፣ ልጅዎት ወይም ሌላ የቤቱ አባል የ U.S. ዜጋ መሆን የለበትም፡፡
12. ***ገቢዬ ሁልጊዜ ተመሳሳይ ባይሆንስ?*** በመደበኛነት የሚያገኙትን መጠን ይግለጹ፡፡ ለምሳሌ በተለምዶ በወር $1000 የሚያገኙ ግን ባለፈው ወር የተወሰነ ስራ ሳይሰሩ $900 ብቻ ካገኙ በወር $1000 እንደሚያገኙ ይግለጹ፡፡ የትርፍ ሰአት ስራ በመደበኛነት የሚያገኙ ከሆነ ያካትቱት፤ አንዳንዴ ብቻ የሚሰሩ ከሆነ ግን አያካትቱት፡፡ ስራ ከሌለዎት ወይም የስራ ሰአትዎ ወይም ክፍያዎት ከተቀነሰ አሁን የሚያገኙትን ገቢ ይጠቀሙ፡፡
13. ***አንዳንድ የቤተሰብ አባላት የሚያሳውቁት ገቢ ባይኖራቸውስ?*** የቤተሰብ አባላት እኛ በማመልከቻው ላይ ምንጠይቀው የሆነ አይነት ገቢ ወይም ምንም አይነት ገቢ አያገኙ ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ እባክዎ ቦታው ላይ 0 ይጻፉ፡፡ ሆኖም ማንኛውም የገቢ ቦታ ባዶ ከተተወ እንደዜሮ ይቆጠራል፡፡ የገቢ ቦታዎችን ባዶ ሲተዉ እባክዎ ይጠንቀቁ፤ አውቀው ያደረጉት ይመስለናል፡፡
14. ***መከላከያ ውስጥ ነን፡፡ ገቢያችንን በተለየ መንገድ እናሳውቃለን?*** መሰረታዊ ክፍያዎት እና ጉርሻው እንደገቢ ማሳወቅ አለብዎት፡፡ ከመኖሪያ በመራቅ የቤት፣ ምግብ ወይም ልብስ አበል በገንዘብ ካገኙ እንደገቢ መካተት አለበት፡፡ ሆኖም ቤትዎ የመከላከያ ቤቶች ወደግል የማምጣት ቅስቀሳ አካል ከሆነ የቤት አበልዎትን እንደ ገቢ አያካቱት፡፡ ከስምሪት የሚገኝ ማንኛውም ተጨማሪ የጦርነት ክፍያ ከገቢ አይካተትም፡፡
15. ***ለቤተሰቤ ማመልከቻው ላይ በቂ ቦታ ባይኖርስ?*** ደረጃ 3 (ብቻ) ይሙሉ እና ከተሞላው ማመልከቻ ጋር ያያይዙ፡፡ ሁለተኛ ማመልከቻ ለማግኘት የልጅዎን የት/ቤት አመጋገብ ሀላፊ ያነጋግሩ፡፡
16. ***ቤተሰቤ ተጨማሪ እርዳታ ይፈልጋል፡፡ ልናመለክትበት የምንችለው ሌሎች መርሀግብሮች አሉ?*** ለ SNAP ወይም ሌላ የእገዛ ጥቅማ-ጥቅም እንዴት ማመልከት እንደሚቻል ለማወቅ የአካባቢ እገዛ ጽ/ቤት ያነጋግሩ ወይም በ **1-877-423-4746**ይደውሉ፡፡
17. ***ልጄ የ CEP ት/ቤት ከተማረ እና ከዛ ወደ የ CEP ያልሆነ ት/ቤት ከተዛወረስ***? ***ተማሪው ወደ የ CEP ያልሆነ ት/ቤት ከተዛወረ ወላጅ ማመልከቻ ማስገባት አለበት፡፡ ማመልከቻው እስኪጸድቅ እስከ 10 ቀናት ድረስ ሊወስድ ይችላል፡፡ ከ CEP ት/ቤት ወደ የ CEP ያልሆነ ት/ቤት የሚዛወሩ ተማሪዎች ምግብ በነጻ እንዲመገቡ 10 ቀናት የእፎይታ ጊዜ ይሰጣቸዋል፡፡ ከ 10 ቀናት በኋላ ተማሪው ወደ ከፋይነት ይለወጣል፡፡ እፎታ ጊዜ ካበቃ በኋላ እና ማመልከቻው እስኪጀመር ድረስ ያሉ የምግብ ክፍያዎች በሙሉ ወላጅ ሀላፊነት ናቸው፡፡***

ሌሎች ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም እገዛ ከፈለጉ **Tansheila Harris፣ የነጻ እና ቅናሽ ተቆጣጣሪ II በ 678-676-1777 በነጻ ይደውሉ ወይም ኢሜል** tansheila_harris@dekalbschoolsga.org

ከሠላምታ ጋር ፣

Dr Connie R. Walker

**ዶ/ር Connie R. Walker፣ የስራ ሀላፊ፣ የ DeKalb ት/ቤት አመጋገብ አገልግሎቶች**

***ይህ ተቋም እኩል እድል የሚሰጥ ነው።***